**መመሪያ ቁጥር 1/2012**

**የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ የትራንስፖርት ዘርፍ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ መመሪያ**

የሚኒስትሮች ኮሚቴ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ አንቀፅ 7 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፣

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ "**የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ የትራንስፖርት ዘርፍ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 1/2012**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

2. **ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) 1/ "**ደንብ**" ማለት የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁ. 03/2012 መስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 466/2012 ነው፤
2) "**ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር**" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
3) "**ባለስልጣን**" ማለት የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም እንደቃሉ አገባብ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ማለት ነው፣

Scanned by CamScanner

4) **"ህግ አስከባሪ"**ማለት የፌደራል ወይም የክልል ፖሊስ ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሀገር መከላከያን እና የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትን እና የዐቃቤ ህግ ተቋማትን ይጨምራል፤

5) **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰ ወይም ይህን መመሪያ የሚያስፈጽሙ አካላት ናቸው፤

6) **"ባቡር"** ማለት የአዲስ አበባ ቀላል የባቡር ትራንስፖርት፤ የኢትዮ-ጂቡቲ የመንገደኞችና የዕቃ ማጓጓዣ ባቡር ናቸው፤

7) **"የመንግስት ተሽከርካሪዎች"** ማለት በመንግስት ባለቤትነት የተመዘገቡ ወይም ይዞታ ስር የሚገኙ ሁሉንም ዓይነት ተሽከርካሪዎች ሲሆን በሠሌዳ መለያ ቁጥር ኮድ-4፤ ኮድ-3፤ ኮድ-2፤ ኮድ-መከ፤ ኮድ-ፖሊስ ወይም በሌላ ማናቸውም ዓይነት መለያ የተመዘገቡትን ያጠቃልላል፤

8) **"የግል ተሽከርካሪዎች"** ማለት ከኮድ 2 ውጪ ያለ በግለሰቦች የተመዘገበ፤ በንግድ ተቋሞች በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፤ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ወዘተ ... የመተዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያጠቃልላል፤

9) **" የቤት ተሽከርካሪ"** ማለት የሠሌዳ ቁጥራቸው ኮድ-2 የሆነ የግል መገልገያ መኪኖች ናቸው፤

10) **"የግል አሰሪዎች"** ማለት የንግድ ተቋማትን፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፤ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን፤ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶችን፤ በአጠቃላይ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያጠቃልላል፣

11) **"ሠራተኛ"** ማለት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ አዋጅ፣ በአሰሪና ሠራተና ጉዳይ አዋጅና በሌሎች ልዩ ህጎች የሚተዳደሩ ሰራተኞችን ያካትታል፤

12) በአዋጁና ደንቡ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጋት ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ።

**3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

Scanned by CamScanner

## ክፍል ሁለት

## የትራንስፖርት፣ የመናኸሪያ፣የወደብ፤ ደረቅ ወደብና ሎጂስቲክስ አጠቃቀም

4. **የሀገር-አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርትን በተመለከተ**

1) ማንኛውም ሀገር-አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በማንኛውም ጊዜ ከተሽከርካሪው ወንበር ብዛት 50% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

2) ሀገር-አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ማጓጓዝ የሚችለው የተሳፋሪ ብዛት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ መሰረት ብቻ ይሆናል፤

5. **የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርትን በተመለከተ**

1) የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት ማለት በደንቡ ውስጥ የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ዓይነት የሠሌዳ መለያ ኮድ ከተማ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎችን፤ አውቶብሶችን፤ የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶችን፤ እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን፤ ባለሁለት እግር ባለሞተርና ሞተር አልባ ሳይክሎችንና በእንስሳ ጉልበት የሚንቀሳቀሱ የትራንስርት አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፤

2) የከተማ ውስጥ አውቶብሶች መጫን የተፈቀደላቸው በመደበኛነት ከወንበር ቁጥር መጠን 50% ብቻ ነው፤

3) የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶች መጫን የሚችሉት የወንበራቸውን 50% ብቻ ነው፤

4) የከተማ ውስጥ ታክሲዎች /በየትኛውም የሠሌዳ መለያ ኮድ የሚሰሩ/ መጫን የሚችሉት በህግ ከተፈቀደላቸው የሠው ብዛት 50% ብቻ ነው፤

5) ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች መጫን የሚችሉት ከአሽከርካሪው በተጨማሪ አንድ ሠው ብቻ ነው፤

6) ባለ ሁለት እግር የሞተር ወይም ሞተር አልባ ሳይክሎች ከአሽከርካሪው ሌላ ምንም ሰው መጫን አይፈቀድላቸውም፤

7) ለሰው ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡት በእንስሳት የሚገፉ ጋሪዎች መጫን የሚችሉት ከባለጋሪው በተጨማሪ አንድ ሰው ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

6. **የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ**

1) የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መንገደኞችን ማጓጓዝ የሚችለው ከዚህ በፊት ሲጫን ከነበረው 25% ብቻ ነው፤

2) በዚህ ምክንያት የሚፈጠረው የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ለመሸፈን የባቡር መስመሩን ተከትሎ በሚሰጠው ተጨማሪ የግል የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሸፈን ይደረጋል፤

3) የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መስመርን ተከትለው አገልግሎ እንዲሰጡ የሚደረጉ የግል የብዙሃን ትራንስፖርት ዘዴዎች መጫን የሚችሉት የመደበኛ ወንበራቸውን 50% ብቻ ነው፤

4) የኢትዮ-ጂቡቲ የምድር ባቡር መንገደኞችን ማጓጓዝ የሚችለው ከመደበኛ የወንበር አቅሙ 50% ነው፤

5) የኢትዮ-ጂቡቲ የጭነት ባቡር በመደበኛ የመጫን አቅሙ መሰረት የጭነት አገልግሎት ሥራውን ያከናውናል፡፡

7. **የመንግስት. የግልና የቤት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ**

1) የመንግስት ተሽከርካሪዎች መጫን የሚችሉት የወንበር ቁጥር 50% ብቻ ነው፤

2) የግልና የቤት ተሽከርካሪዎች መጫን የሚችሉት ከአሽከርካሪዉ ውጪ የወንበር የመጫን አቅማቸውን 50% ብቻ ነው፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ለዚህ መመሪያ ወይም ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወይም ለደንቡ አፈጻጸም፤ ወይም ለሀገርና ህዝብ ደህንነት ስራዎች አገልግሎት የሚሰጡትን የሀገር መከላከያ፤ የፖሊስ፤ የአምቡላንስ፤ የእሳት አደጋ እና የመንግስት መኪኖች የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንባቸውም፡፡

8. **የጭነት ተሽከርካሪን በተመለከተ**




Scanned by CamScanner

የጭነት ተሽከርካሪዎች መጫን የሚፈቀድላቸው ከአሽከርካሪው በተጨማሪ አንድ ሠው ብቻ ነው፡፡

9. **ለትራንስፖርት አገልግሎት የተፈቀደ ሰዓትና የታሪፍ ጭማሪን በተመለከተ**

1) ማንኛውም ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚቻለው ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፤
2) ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎቶች ሲሰጡ የሚያስከፍሉትን የታሪፍ ጭማሪ በተመለከተ ከመደበኛ ዋጋው 50 ከመቶ ጭማሪ የሚኖረው ሆኖ ዝርዝሩ በባለስልጣኑ ይወሰናል፤
3) የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ክልሎች ከየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የየከተሞቻቸውን የትራንስፖርት አገልግሎት የስራ ሰዓት ገደብ ይወስናሉ፤
4) የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍን በተመለከተ የክልል ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ባለስልጣን ከየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የየከተማውን የትራንስፖርት ታሪፍ ይወስናሉ፡፡

10. **የቤት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀምን በተመለከተ**

1) በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የቤት ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የሚቻለው የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ሙሉ ቁጥር ወይም ጎዶሎ ቁጥር በሚል እየተለየ ሲሆን የሠሌዳው የመጨረሻ ቁጥር ሙሉ ቁጥር የሆነ የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎች ብቻ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን መንቀሳቀስ የሚችሉ ሲሆን በዚህ ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ጎዶሎ ቁጥር የሆነ የቤት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ አይፈቀድላቸውም፡፡ የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ዜሮ የሆነ የግል መኪኖች እንደ ሙሉ ቁጥር ይወሰዳሉ፤
2) እንዲሁም በሚቀጥለው ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ጎዶሎ የሆነ የግል ወይም የቤትተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ የሚፈቀድላቸው ሲሆን በዚህ ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ሙሉ ቁጥር የሆነ የቤትተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ አይፈቀድላቸውም፤፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ከስራቸው ጸባይ አንጻር በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፤ በደንቡ ወይም በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ውስጥ የተገለጹት ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ ሰዎች ከባለስልጣኑ በሚሰጣቸው ልዩ የይለፍ ፈቃድ ብቻ እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

11.<u>የመናኸሪያዎች አጠቃቀም</u>

1) በየትኛውም ቦታ የሚገኙ መናኸሪያዎች ማስተናገድ የሚችሉት የየዕለት ስምሪት ከመደበኛው ጊዜ የስምሪት መጠን 50% ብቻ ነው፤

2) የሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በየመናኸሪያዎቹ በተመሳሳይ ሰዓት ደርሰው ለሰዎች ንክኪ እና መጠጋጋት ዕድል እንዳይፈጥሩ የአጭር ርቀትና የረዥም ርቀት የህዝብ ማመላለሻዎች መናኸሪያ የመግቢያና የመውጫ ሰዓት እንዲለያይ ይደረጋል፤

3) በየመናኸሪያዎቹ ላይ አገልግሎት የሚያገኙ ተሳፋሪዎች የጤና ሚኒስቴርና የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ወይም በክልች የሚገኙ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በሚያዘጋጁት ቅጽ መሰረት የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፤ የየመናኸሪያዎቹ የስራ ኃላፊዎች ይህን ተግባር የማከናወን ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፤

4) መናኸሪያዎችን የጸረ-ተህዋሲ ኬሚካሎችን እንዲረጩ ይደረጋል፤

5) እያንዳንዱ መናኸሪያ በጤና ሚኒስቴርና በህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትወይም በክልች የሚገኙ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሚዘጋጁትን የመከላከያና የጥንቃቄ መመሪያዎች በጉልህ ስፍራ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

6) በሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ላይ በጉዞ መነሻ እና መድረሻቸው ላይ የጸረ-ተህዋሲ ኬሚካሎችን እንዲረጩ ይደረጋል፤

7) በየመናኸሪያዎች ውስጥ የሚገቡ ተገልጋዮች የሙቀት መጠናቸው እንዲለካ እና ከመሳፈራቸው በፊት የእጅ ንጽህናቸውን እንዲጠብቁ ይደረጋል እንዲሁም የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለባቸው

8) የደንቡ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የጭነት ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪዎች፤ ገንዘብ ተቀባዮችና ረዳቶቻቸው የመተንፈሻ አካል መከለያ /ፌስ ማስክ/ እና የእጅ ጓንት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

9) በዚህ የጥንቃቄ ትግበራ ወቅት ማንኛውም የኮቪድ-19 ምልክት የታየበት ሰው በአቅራቢያው ወደተዘጋጀው የለይቶ ማቆያ ማዕከል በጤና ባለሙያዎች አማካኝነት እንዲወሰድ ይደረጋል፤

Scanned by CamScanner

12.<u>የወደብ፤ ደረቅ ወደብና ሎጂስቲክስ አጠቃቀም</u>

1) የሀገራችን የሎጂስቲክስ አገልግሎት እንዳይስተጓጎል የወደብ አገልግሎት ከምናገኝባቸው ጎረቤት ሀገራት ጋር ቅንጅት በመፍጠርና ይህን አገልግሎት በሚመለከት ልዩ ግብረ-ኃይል በማቋቋም ከሃገራቱ ተመሳሳይ መዋቅሮች ጋር እንዲሰራ ይደረጋል፤

2) በሀገራችን ደረቅ ወደቦች እና መጫኛ ወይም ማውረጃ መጋዘኖች የሎጂስቲክስ አገልግሎት ስርዓትን ሲያከናውኑ የሠራተኞችን፤ የተገልጋዮችን እና የጫኝና አውራጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል መልኩ ፕሮግራም አውጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል።

## ክፍል ሶስት

## የሰራተኞች የስራ መግቢያና መውጫ ሰአት

13.<u>የሠራተኞች የሥራ ሰዓት</u>

1) ማንኛውም በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በተቋሙ ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ስለቫይረሱ አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች ላይ ቢያንስ እጅ ለመታጠብ የሚያስችል ውሃና ሳሙና ማዘጋጀት ፣ በተቻለ መጠን ሌሎች የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2) ማንኛውም በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በተቋሙ ስር የሚገኙ ሰራተኞች በአንድ ክፍል ውስጥ፣ በአንድ መስሪያ ቦታ ወይም በአንድ ትራንስፖርት ውስጥ ተጨናንቀውና አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በማያስችል መልኩ እንዳይሰሩ ለማድረግ አስፈላጊውን ፈረቃ ማመቻቸት፤ ሰራተኞቹ ቤታቸው ሆነው የሚሰሩበትን ሁኔታ ወይም እረፍት በመውሰድ ስራ ቦታ እንዳይመጡ የማመቻቸት ሀላፊነት አለበት።

3) ማንኘውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግስት ተቋምና በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት የሚተዳደሩ ሰራተኞችን የሚስተዳድር የግል ድርጅት ሰራተኞቹ ወደ ስራ ቦታ ለመሄድ ትራንስፖርት መጠቀም አስፈላጊ ከሆነ በስራ ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት የማመቻቸት ሀላፊነት አለበት።




Scanned by CamScanner

4) የፌደራል ሠራተኞች ሥራ መግቢያ ሰዓት ከጠዋቱ 1:30 ሲሆን ከስራ መውጫ ሰዓት ደግሞ ከቀኑ 9:30 ይሆናል፤

5) ይህ የሥራ ሰዓት ሽግሽግ ሠራተኞቹ በስራ ሰዓት መካከል የሚያገኙትን የእረፍት ጊዜ አያሳጣቸውም፤

6) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ በመንግስት የፋይናንስ ተቋማት፤ በመንግስት የህክምና ተቋማት፤ በትራንስፖርት መናሃሪያ ሠራተኞች፣ በገቢዎች ሚኒስቴርና ጉምሩክ ኮሚሽን ሰራተኞች እና የህግ ስከበሪ ተቋማት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፤

7) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌ ከመደበኛው የስራ ሰዓት ውጭ በሽፍት ፈረቃ ሰዓት የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚነት የለውም ፡፡

## 14.<u>የክልል መስተዳድር ሠራተኞች የሥራ ሰዓት</u>

በህገ-መንግስቱ ውስጥ ክልሎች ተብለው የተዘረዘሩት ክልሎች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት በሚመለከት የዚህን መመሪያ ዓላማ ሳይቃረን ክልሎች ከየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አሰራር እንዲዘረጉ ይደረጋል፡፡

## 15.<u>የግል አሰሪዎች ሠራተኞች የሥራ ሰዓት</u>

1) የግል አሰሪዎች የሥራ መግቢያ እና መውጫ ሰዓት እስከአሁን ድረስ የሚጠቀሙበት መደበኛው የሥራ ሰዓታቸው እንዳለ ይቀጥላል፤

2) በደንቡ ላይ የተደነገጉት እና የዚህ መመሪያ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሠራተኞቻቸውን ከመደበኛው የስራ ሰዓት ውጭ በሽፍት የፈረቃ ሰዓት የሚያሰሩ የግል አሰሪዎች ይህ የስራ ሰዓት ሽግሽግ አይመለከትም፤

## 16.<u>የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞ የስራ ሰዓት</u>

1) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞች የስራ መግቢያ ሰዓት ከጠዋቱ 3:30 ሲሆን ከስራ መውጫ ሰዓት ደግሞ ከቀኑ 11:30 ይሆናል፡፡ ይህ የሰዓት ሽግሽግ ሠራተኞቹ በስራ ሰዓት በመሃል የሚያገኙትን የእረፍት ጊዜ አያስቀርባቸውም፡፡

Scanned by CamScanner

2) የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞች የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት በተመለከተ መስተዳድሩ ከነባራዊ ሁኔታው አንጻር በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት ይወሰናል።

## ክፍል አራት

## ግብረሀይል ስለመቋቋም

**17.<u>የኮቪድ-19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም ግብረ-ሃይል ስለማቋቋም</u>**

1/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉትን ተግባራት ለመከታተልና ለማስፈጸም የሚያስችል በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የሚመራ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ የሆነ ግብረ-ሃይል በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፤

**2/ <u>ግብረ-ሃይሉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-</u>**

ሀ. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር - ሰብሳቢ

ለ. የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተወካይ - አባል

ሐ. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ - አባል

መ. የፌደራል ሲቪል ሰርሲስ ኮሚሽን ተወካይ--አባል

ሠ/ አንድ የተለየ ክልልን በሚመለከት ጉዳይ ላይ የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ወይንም በእርሱ የሚወከል - አባል ናቸው።

3/ የግብረ ሀይሉ ስልጣንና ተግባራት፡-

ግብረሀይሉ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

1. የዚህን መመሪያ አፈጻጸም በበላይነት ይከታተላል፤
2. በየጊዜው አፈጻጸሙን ይገመግማል፤
3. ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፤
4. ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣
5. ሌሎች ከሚኒስትሮች ኮሚቴ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን ይቀበላል፣ ይተገብራል፡

4/ ግብረ-ሃይሉ የሚሰበሰብበትን ጊዜና አሰራሩን እራሱ በሚያወጣው የአሰራር ስርዐት ይወስናል፤

5/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ የግብረ-ሃይሉን አባላት ቁጥር ወይም ስብጥር ሊቀይር ይችላል።

**18.<u>ቴክኒካል ኮሚቴ</u>**

1/ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚዋቀር የኮቪድ-19 ትራንስፖርት ቴክኒካል ኮሚቴ ይቋቋማል፤

2/ የኮሚቴው ስልጣንና ተግባር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሰረት በተቋቋመው ግብረ-ሃይል ይወሰናል፤

3/ የቴክኒካል ኮሚቴው ተጠሪነት ለግብረ-ሃይሉ ይሆናል።

**19.<u>የክልል ግብረ-ሃይል አደረጃጀት</u>**

በሁሉም ክልሎች ውስጥ ይህን የአፈጻጸም መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ግብረ-ሃይል የፌደራሉን ግብረ-ሃይል አደረጃጀት ተከትለው ያቋቁማሉ።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**20.<u>ተጨማሪ የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቋቋመው ግብረ-ሃይል የዚህን መመሪያ አፈጻጸም የሚመለከቱ ተጨማሪ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በየጊዜው እየቀረጸ ተግባራዊ ማድረግ ይችላል።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The ... Democratic Republic ... Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

**21.<u>አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን በተመለከተ</u>**

በደንቡ ያለተመለከቱና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ድንጋጌዎች በተጣሱ ጊዜ አግባብነት ያላቸው የትራፊክ ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**22.<u>የጭነት ተሽከርካሪን በተመለከተ</u>**

1) በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ውስጥ የተደነገጉት ክልከላላ ገደቦች የደረቅ እና የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም።
2) የጭነት ተሽከርካሪዎች በየትኛውም የሀገራችን ክፍል መደበኛ ስራቸውን ማከናወን ይችላሉ።

**23.<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሁሉም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት።

**24.<u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜት</u>**

1/ ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በሚኒስትሮች ኮሚቴ ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

2/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተፈጻሚነት ዘመን ውስጥ ይህን የአፈጻጸም መመሪያ ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ከተከሰቱ መመሪያው በሚኒስትሮች ኮሚቴ ሊሻሻል ይችላል፤

3/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ የዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት አብሮ ያበቃል።

**ሚያዝያ 5 ቀን 2012 ዓ.ም**

**የሚኒስትሮች ኮሚቴ**



Scanned by CamScanner